# ከትርጉም አክሮባት እና ከቅጽል ባሻገር ኤች አር ሲመነዝር
## (ኤች አር ለምን? ኤች አር ለማን? ኤች አር የማን ?)

**ከዘሪሁን ተሾመ**

የፖለቲካ መድረካችን የሰሞኑ አንድ ዋነኛ ጉዳይ «የኢትዮጵያ የዴሞክራሲና የተጠያቂነት አዋጅ» በሚል በአሜሪካ ኮንግሬስ ረቂቁ በቅርቡ የተንሸራሸረው ሰነድ ነው፡፡ በውስጥና በውጪ የሚገኙ ምሁራኖቻችን፤ የመንግስትና የፓርቲ መሪዎቻችን፤የተለያዩ ተንታኞችና ኤክስፐርቶች ወዘተ. ይህንኑ ጉዳይ አንስተው ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል፤ እየሰነዘሩም ይገኛ ሉ፡፡ ክርክሩና ተሳትፎው ይበል የሚባል ቢሆንም ለሚታይና ለሚጨበጥ ውጤት ሊያበቃን ይገባል፡፡ የተናጠል አቋምን፤ ልዩነታችንን እና ተጋሪነታችንን በግልፅ ላስቀመጠ መግባባት በሚያበቃ የተሻለ ግንዛቤ የሚገለፅ ውጤት፡፡

በዚህ ፀሐፊ እምነት ለዚህ መሰል ውጤት እንድንበቃ የሚያስችሉ ተፈላጊ ነጥቦች በእስካሁኑ ክርክር ተነስተዋል፡፡ በቂ ማብራሪያም ቀርቧል፡፡ ሆኖም የኤች አር 2003 ጉዳይ ለተወሰኑ መለኮታዊነትን የሚጠጋ አዎንታዊነት ያለው የቀና አጋር ተግባር ሆኖ ይታያል፡፡ ለተወሰኑ ሌሎች ደግሞ የተጀመረውን የዴሞክራሲ ሂደት የሚያግዝ ሳይሆን የሚገዘግዝ፤ የኢትዮጵያ ህዝቦች ብሔራዊ ጥቅም ፀር፤ የሁለቱ ሀገራት ወዳጅነት ፀር፤ ወዘተ. የሆነ አፍራሽ ቀመር ተደርጎ ይቀርባል፡፡ የብዙዎች ክርክርም በመረጃ እና ምክንያታዊነት ከተደገፈ ተገቢ ወገንተኛነት ይልቅ ጥሬ ፍላጎትና ምኞት ላይ የተንጠለጠለ ትርጉም/ንባብ የሚነዳው ነው፡፡ የቃላት አክሮባት፣ የቅፅል ድርደራ እንዲሁም ፉከራ ያጀበው የራስ ሽንገላ ለብዙ ተከራካሪዎች አይቀሬ የሆነ ብቸኛ ምርኩዝ ሆኖ ያጋጥማል፡፡ በዚህ መሰል የክርክር ሂደት ደግሞ የምክንያታዊነት፣ የመረጃ እና የጥሬ ሀቅ እጥረት ያለባቸው «ጭፍን ተሟጋቾች» ተፈላጊ እና መሸሸጊያ አግኝተው የማይገባቸውን ቀጣይነት ይጎናፀፋሉ፡፡ በአዲስ ነገር ጋዜጣ የጥቅምት 23 እትም በክርክር አምድ «የአሜሪካ ኮንግሬስ አዎንታዊ እርምጃ» በሚል ዳግማዊ የተባሉ ፀሐፊ ያቀረቡት «ክርክር» በተለይ ከዚህ በተያያዘ ጥሩ አስረጂ ነው፡፡

ሁላችንም (ኢትዮጵያዊያን) የውጤቱ ተቀባዮች በሆንንበት በዚህ ጉዳይ ዙሪያ የሚደረገው የሀሳብ ልውውጥ ፍሬያማ እንዲሆን የረቂቁ ትክክለኛ ይዘት ሊገላለጥ ይገባል፡፡ በዚህ ላይ በመመስረትም የድጋፍ ወይም ተቃውሞ መሰረት የሆኑ ትርጓሜዎች ተጣጣሚነት መመዘን ይኖርበታል፡፡ የዚህ ፅሑፍ መነሻ እና ዓላማም ይህ ነው፡፡ ኤች አር ለምን? ለማን? እና የምን አጋር ወይም ፀር ነው? በርግጥ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲና ሉዓላዊነት አጋር ነው? የኢትዮጵያና አሜሪካ የተናጠልና የጋራ ደህንነትን የማገዝ ግብ ያለው ነውን? በርግጥ የተደጋጋፊ ተጠቃሚነት አጋዥ ግብዓት ወይስ ይህን የሚሸረሽር ውጤት ያለው ነው? እንዴት? ለምን?

## ተገቢ መነሻ፡ የረቂቁ መሰረታዊ መርሆዎች እና ትርጓሜ

ሁላችንንም ሊያግባባ የሚችል አንድ የመነሻ ሀቅ አለ፡፡ ይህም ትኩረታችን ያረፈበት የአሜሪካ ኮንግሬስ ኢትዮጵያን የተመለከተ ረቂቅ አዋጅ/ቢል፣ ኤች አር 2003 በሚል የሚታወቅ አንድ እና አንድ ብቻ ሰነድ ነው፡፡ በዚህ አንድ ሰነድ ላይ ግን ሁለት የተራራቀ አቋም፤ የግንዛቤ ልዩነት እንዲሁም በግለ ተቃርኖ የተሞላ የሚገርም መተላለፍ አለ፡፡ ግለተቃርኖውና ልዩነቱ ስለረቂቁ አንድ ትርጉም እንጋራለን በሚሉ አቀንቃኞች መካከል እና ክርክር ውስጥ ሳይቀር የሚያጋጥም ነው፡፡ ለዚህ መንስኤው የረቂቁ «ደጋፊ» እና

«ተቃዋሚ» ነን ከሚሉ ክፍሎች አንድን ሰነድ ከሚያጣቅስ የትርጓሜ ልዩነት ብቻ የመነጨ፤ ወይም/እና ከረቂቁ አቀማመርና ከቀማሪዎቹ ፍላጎት የተያያዘ ጭምር መሆን አለመሆኑ መፈተሽ ይኖርበታል:: ከዚህ አንፃር የኤች አር 2003 ትርጓሜም ሆነ ግንዛቤ ትክክለኛነት እና ተጣጣሚነት መስፈርት መሰረታዊ የሆነው የረቂቅ ሰነዱ ይዘት ብቻ መሆን አለበት::

ለዚህ አግባቢና አካታች የሆነ ቀረቤታ ያለው የሰነዱ አካል ደግሞ ለሀሳቡ መነሻ መሰረት እና መድረሻ ግብ ሆኖ የተቀመጠው የረቂቁ ዓላማ ነው:: በተለይም (ዳግማዊ የተባሉት ፀሐፊ በዚሁ በአዲስ ነገር ተርጉመው ያቀረቡትን በቀጥታ በመዋስ) በረቂቁ ሰነድ ተራ ቁጥር 1 የፖሊሲ ግቦች በሚል የተቀመጠው ነጥብ ይገልፀዋል:: ይህ ነጥብም ***«በኢፌዴሪ ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ዴሞክራሲ፣ የዳኝነት ነፃነት፣ የፕሬስ ነፃነት፣ የሰላም አስከባሪ አቅም ግንባታ እና የኢኮኖሚያዊ ልማት እንዲጎለብት ማገዝ»*** የሚል ነው:: በዚህ ስር የቀረበው ገለፃ የረቂቁ ትኩረት ያረፈበትን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ወዘተ. በተመለከተ ከባለቤትነት፣ ከአተገባበር፣ ከመሠረታዊ ድርጊቶች ግንዛቤ ወዘተ. በተያያዘ ታሳቢ የተደረጉ ገዢ መርሆዎችና ፅንሠ ሀሳቦች የያዘ ነው:: በመሆኑም በረቂቁ ደጋፊና ተቃዋሚ ክፍሎች አቋም ደረጃ ብቻ ሳይሆን በሰነዱ ዋና አርቃቂዎች ፍላጎት ብሎም ዓላማውንና አፈፃፀሙን አስመልክቶ ባካተታቸው ገለፃዎች መካከል ከእነዚህ የተቆራኘ ተጣጣሚነት መኖር አለመኖሩን ለማየት ያመቻል:: ምክንያቱም ከውጪ የተጫነ ሳይሆን ከረቂቁ ከራሱ የመነጨ በመሆን ማንም ልግፋው ቢል የሚያዳግት መሰረታዊ አግባቢነት ያለው ማጣቀሻ ይፈቅዳልና::

በነፃነትና በዕድገት የታጀበ የተረጋጋ ሀገራዊ ህይወትን ለሚመኝ ማንኛውም አንባቢ ይህ የረቂቁ ዓላማ፣ ይዘትና ገለፃ እጅግ ቀና የመነሻ እምነት፣ የመድረሻ ግብ እና አተገባበር አመላካች ነው:: ከዚህ የረቂቁ ነጥብ ብቻ ከታየ ኤች አር 2003 አፍራሽ ፍላጎት ወይም ዓላማ ያለው ነው ብሎ መደምደም ይቅርና መጠርጠርም የከበደ ይሆናል:: የዛኑም ያህል ከአጋር ወዳጅ ለበጎ ግብ የታቀደ ረቂቅ ነው የሚል አስተያየት ለመስጠት በበቂ ያደፋፍራል:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን በሁለቱም ደረጃ ፍፁማዊ ድምዳሜን ወይም ብይን ለማሳለፍ ተገቢም ሆነ ተቀባይ መሰረትን አይቸርም:: ምክንያቱም ከወደፊት ተግባር ውጪ ረቂቁ በዚህ አንድ ገለፃ ደረጃ ያዘለውን የቀና መነሻ እና የአጎልባች ውጤት ታሳቢነት የሚመጥን የአፈፃፀም ስልት እና ፕሮግራም፣ ከዚህ ተጣጣሚ ሆኖ የሚመጥን የማያሻማ ትርጉም እና የገላጭ ቃላት ምርጫ ሊኖረው የገባል:: ይህም በተጨባጭ አስረጂ ተደግፎ የሚታይና የሚረጋገጥ መሆኑ ግድ ነው:: ዋነኛ መነሻውም የረቂቁ መሰረታዊ ይዘት (ምንነት ወይም ህልውና) እነዚህን የተለያዩ ክፍሎች እንደ አንድ ውትድ አጣጥሞ ያቀናጀ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው:: በቅድሚያ በረቂቁ ዓላማ የተካተቱ አከራካሪ ያልሆኑ መሰረታዊ ነጥቦች እንመልከት::

የረቂቁ ዓላማ በተቀመጠበት ዓረፍተ ነገር ውስጥ በገላጭነት ከጥቅም ላይ የዋሉ ሁለት ቁልፍ ቃላት እናገኛለን-- ***«እንዲጎለብት»*** እንዲሁም ***«ማገዝ»*** የሚሉ:: እነዚህ ቃላቶች ማጎልበት እና እገዛ የሚሉ የድርጊት ብሎም የመርህ አመላካች ፅንሰ ሀሳቦችን የሚወክሉ ከመሆናቸውም በላይ ረቂቁን በተመለከተ ለሚታየው የማን (ባለቤትነት እና ሉዓላዊነት የሚነካ)፤ ለምን (የመነሻ ምክንያትና የግብ ምንነት የሚነካ)፤ እንዲሁም እንዴት (የአፈፃፀም ዘዴና ስልት የሚነካ) የትርጉም ክርክር ምክንያታዊነትን እና ተገቢነትን ከዋናው ምንጭ አጣቅሶ ለመመዘን በረቂቁ ታሳቢ የተደረገ ትርጉምና መርህ በተሻለ ማየት ያስችላል::

ከዚህ በተያያዘ ምላሽ የሚያገኝ መሰረታዊ ጥያቄ ቢኖር «የረቂቁ ትኩረት ያረፈበት ***የማን ዴሞክራሲ፣ የማን ልማት፣ የማን ሰብዓዊ መብት*** ወዘተ. ነው?» የሚለው ነው:: አሻሚ ያልሆነው ምላሽ ደግሞ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚል ሆኖ እናገኘዋለን:: (የአሜሪካ ወይም ሽራፊ ሉዓላዊነት ያላት ፖርቶሪኮ ዴሞክራሲና ልማት አይደለም::) ***ለምን ትኩረት ተደረገበት*** ለሚለው በረቂቁ ተቀምጦ የምናገኘው ምላሽ ደግሞ «ግንኙነት ስላለን፣ ወዳጅ በመሆናቸው ወይም አጋር በመሆናቸው» የሚል ነው:: እንጂ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ «ተረጂዎች በመሆናቸው፣ ወይም እርዳታችንን ተቀባይ በመሆናቸው ወይም የምናስተዳድራቸው ኮሎኒዎች» የሚል አይደለም:: በረቂቁ በተራ ቁጥር 5 እና 6 የሁለቱን ሀገሮች ግንኙነት አስመልክቶ የተጠቀሰው ይህንኑ የሚያጠናክር ነው:: ከዚሁ ተያይዞ ***ምን እንዲሆን ወይም ምን ለማድረግ*** ለሚለው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽም «የኢትዮጵያ ዴሞክራሲና ልማት እንዲጎለብት» የሚል እንደሆነ ማየት ይቻላል::

የአተገባበሩ ወይም ***የአፈፃፀሙን ዘዴ/ስልት*** ዋና ባህሪ በተመለከተም ቁልፍ የሆነው ገላጭ ምላሽ ***«ማገዝ»*** የሚል ነው:: ይህ ደግሞ መተጋገዝን፣ ታሳቢ ያደረገ ነው:: ***«ማጎልበት»*** የሚለው ቃልም «የተጀመረና በመካሄድ ላይ ያለ፣ በተወሰነ ደረጃ የተከናወነና በመከናወን ላይ ያለ» ሂደት ወይም ድርጊት መኖሩን እውቅና መስጠትና ታሳቢ ማድረግን ያመለክታል:: ይህን አስመልክቶ ከረቂቁ ሊጎተት የሚችል ልዩነት ካለ ታሳቢ የተደረገው ክንውን ወይም ድርጊት ምን ያህል ነው የሚለውን የመጠን ልዩነት የተመለከተ ከመሆን የወጣ ሊሆን አይችልም:: የፈለገውን ያህል የአማርኛ አጠቃቀማችን ከፖለቲካዊ ዕይታችን በተያያዘ የተለያየ ነው ቢባል ***«ማጎልበት»*** የሚለው ቃል በየትኛውም ደረጃ ***ያልነበረ እና የሌለን መፍጠር*** የሚል ትርጓሜ የለውም፤ አይኖረውም፤ ሊኖረውም አይችልም::

ከፍ ሲል ከጠቀስነው የረቂቁ ዓላማ ያወጣናቸው እነዚህ ትርጓሜዎች ሰፋ ባለ ደረጃ ያዘሉት የመሰረታዊ ታሳቢዎች ምልከታ አለ:: ይህም በዋናነት የረቂቁ ትርጓሜ ክርክር እምብርት በሆነው የባለቤትነት እና የሉዓላዊነት ጉዳይ ዙሪያ ተጨማሪ ብርሃን የሚፈነጥቅ ነው:: ***የረቂቁን ዓላማ ለማስፈፀም ታሳቢ ያደረገው «መተጋገዝ» በተግባሩ የሚሳተፉ ወይም መሳተፍ ያለባቸው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ክፍሎች የመኖራቸው እውቅና አመላካች ነው::*** በዚህ ረገድ መጠቀስ ያለበት በረቂቁ ታሳቢ ተደርጎ እውቅና የተሰጠው አንድ ጉዳይ ***የሁለቱ ወገኖች ግንኙነት አጋራዊ*** እንጂ ***የጌታና ሎሌ*** አለመሆኑን፤ ለታቀደው ተግባርም ተፈፃሚነት በጎ ፈቃድና ዝግጁነት እንዳለ እውቅና የሚሰጥ መሆኑ ነው:: ከዚህ ውጪ እነዚህ ክፍሎች ወጥ ወይም የተለያየ ህልውና ያላቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚክድ እንደምታም ሆነ ጭብጥ የለውም::

ከእነዚህ መሰረታዊ ነጥቦች ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ከባለቤትነትና ሉዓላዊነት ጋር የሚያያዝ ጥያቄ ህልውናን የተመለከተ ነው:: «እንዲጎለብት እና እንዲታገዝ የተፈለገው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲና ልማት ***ህልውና*** የአሜሪካ ወዳጅነትን ጨምሮ የዓለም አካል ከመሆን የተያያዘ ቢሆንም፤ በዋናነት የተመሰረተው እና የሚያረጋገጠው የተወሰነ ሀገር (ኢትዮጵያ) ስርዓትና መቼት ውስጥ የሚገኝ ሂደት በመሆኑ ነው ወይስ አይደለም?» የረቂቁ ትኩረት ያረፈበት ዴሞክራሲና ልማት ንብረትነቱ የኢትዮጵያ መሆኑ በማያጠያይቅ መልኩ እስከተቀመጠ ድረስ ይህን ለማጎልበትም ሆነ እንደ አዲስ ለመጀመር ተፈላጊ የሆነው ህልውና በዋናነት የሚረጋገጠው የንብረቱ ባለቤት የሆነው ህዝብና ሀገር በሚወስደውና በማይወስደው እርምጃ መሆኑ ምርምር አይሻም:: ከዚህ አንፃር ረቂቁ በጠቀስነው የዓላማ ገለፃው ይህን የሚፃረር ገዢ መርህ ታሳቢ አድርጎ አላስቀመጠም::

ከረቂቁ ዓላማ በመምዘዝ ያወጣናቸው ታሳቢ የተደረጉ መርሆዎች እና ትርጓሜዎች ህልውናን፣ ባለቤትነትን፣ ተሳታፊነትን ወዘተ. የተመለከተ አዎንታዊና ቀና መነሻን

ያመለክታሉ:: ይሁንና ከዚህ ባለፈ በመለጠጥ ይህን የረቂቁ አጠቃላይ ምንነት ገዢ መገለጫ ነው ብሎ ለመበየን ተጨማሪ እርከን ማለፍን ይጠይቃል:: ይህም በረቂቁ ዓላማ አንድ ገለፃ ውስጥ ያገኘነው ቀና ትርጓሜ ኤችአር 2003 በምንለው ውትድ ሰነድ ክፍሎች በአጠቃላይ ይህንኑ የሚመጥን ተጣጣሚ ይዘት የለው ሆኖ መገኘት አለበት ማለት ነው:: ይህ ነው ወይ? ስንባል «የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል» የሚለውን ሀገሪኛ አባባል በጥቅል ደጋፊነት በመንተት አዎ ብለን የድጋፍ ዜማ ማዜም ይቻላል:: በተመሳሳይም «የሲያል ጥርጊያ በቅዱስ ሀሳቦች ይመቻቻል» የሚለውን የፈረንጂኛ ብኂል በመንተት አለመሆኑን በድፍኑ አስቀምጠን ረቂቁን መቃወም ይቻላል:: ሁለቱም ግን በመረጃና ምክንያታዊ ትንታኔ የተደገፈ ተገቢ የትርጓሜ ተጋሪነትና ተጣጣሚነት ከሰነዱ ጋር ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም:: ስለሆነም ምክንያታዊነትና መረጃ ለሚደግፈው ተገቢ ድጋፍ ወይም ተቃውሞ ዋናው አግባቢ መለኪያ አንድ ብቻ ነው:: ኤች አር 2003 የተባለው ሰነድ አካል ሆነው የተቀመጡ የማስፈፀሚያ ስልቶች እና የተግባር ገላጭ ፅንሰ ሀሳቦች በተጠቀሰው የረቂቁ ዓላማ ታሳቢ መርሆዎችና ትርጓሜዎች የሚጣጣሙ መሆን አለመሆናቸው ነው:: ይህ ሲሆን የሚቀርቡ ክርክሮች (የድጋፍ ወይም ተቃውሞ) ከራስ ምኞትና ትርጉም የሚነሱ ወይም ከረቂቁ ምሉዕ ይዘት የሚጣቀስ መነሻ እንዳላቸው በግልፅ ይወጣል:: ቀጥሎ ይህን እንመለከታለን::

**ኤች አር:- በአጋርነትም፣ በታዛዥነትም የማይተገበር...?**

በእርግጥ ኤች አር 2003 በአዲስ ነገር ጋዜጣ የተጠቀሱት የረቂቁ ደጋፊዎች እንደሚሉት «ወዳጅ ሀገርን ለማረቅ ... እና ወዳጅነትን ለመቀጠል» (ፕ/ር አለማየሁ እና አቶ ሳሙኤል እንዳሉት) የተፈፀመ፤ ይህም በመሆኑ ... «የኢትዮጵያ መንግስት እተገብረዋለሁ የሚለውን ዴሞክራሲ እና ህግ ከማክበር ውጪ ምንም የተለየ ነገር የሌለው...» (የአ.አ.ዩ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር ዶ/ር ኤርሚያስ እንዳሉት) ረቂቅ ሰነድ ነው ወይ? ረቂቁን እንደ እነዚህ ምሁራን መደገፍን የሚጋሩት አቶ ዳግማዊ በአዲስ ነገር ጋዜጣ ተመሳሳይ እትም ያቀረቡትን የሰነዱ ዋነኛ ክፍሎች የአማርኛ ትርጓሜ እንዳሉ በመውሰድ ሲመዘን አባባሉ ከፍ ሲል ከጠቀስነው የረቂቁ ዓላማ ገለፃ ተነስቶ የተለጠጠ ቁንፅል ድምዳሜ አሊያም ሌላ የኤች አር 2003 ሰነድ ንባብ ወይም ፖለቲካዊ ፍላጎትን የተንተራሰ ምኞት ከመሆን ያለፈ ተያያዥነት የለውም:: ይህንንም በሚከተሉት ከሰነዱ የአፈፃፀምና የፕሮግራም ክፍሎች በተወሰዱ ማሰየት ይቻላል::

ከኤች አር 2003 መሰረታዊ የራስ ችግሮች መካከል በቅድሚያ ሊጠቀስ የሚችል ቢኖር «ሊያጎለብት» አልሞ «ሳግዘው ተነስቻለሁ» የሚለውን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲና ልማት አጋርነት ለማስፈፀም እንዲሁም የአፈፃፀሙ ማረጋገጫ በሚል ያስቀመጣቸው ስልቶችና መለኪያዎች ይህንኑ የሚቃረን መነሻና መርህ የሚያመለክት ይዘት እና ትርጓሜ ያዘሉ መሆናቸው ነው:: በዚህ ረገድ የረቂቁ ተቃርኖ መሰረታዊነት ገላጭ ነጥብ የረቂቅ ህጉ ማስፈፀሚያ ተመራጭ መንገድ ሆኖ የቀረበው በእገዳና ገደብ (የጉዞ ገደብ፣ የደህንነትና መሰረታዊ ያልሆኑ እርዳታዎች ድጋፍ እገዳ) የሚገለፅ ጫና መሆኑ ነው:: በየትኛውም የቋንቋ አጠቃቀም በረቂቁ ዓላማ የተቀመጠው መተጋገዝ ወይም እነ ፕ/ር አለማየሁ የሚያነሱት «ወዳጃዊ ማረቅ» በአፈፃፀም ደረጃ ይህን ዓይነት የአስገዳጅና የተገዳጅ ግንኙነትን የተመረኮዘ ትርጓሜ/ምንዛሬ ይዘው ሊገኙ አይችልም:: ምክንያቱም ወዳጅነትን የተንተራሰ ማረቅም ሆነ ማጎልበትን ያለመ መተጋገዝ አጋራዊ እንጂ አቅም እና የበላይነትን የተንተራሰ አስገዳጅ ግንኙነት አመላካች አይደለምና:: በመሆኑም አርቃቂዎቹ የረቂቁን አላማ የረሱት ብቻ ሳይሆን እያወቁ ያፈረሱት በዚህ ደረጃ ጭምር ነው::

ከዚህ በተጨማሪም የቢሉ አላማ የሆነውን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲና ልማት መጎልበት አመላካች ተደርገው የተቀመጡት (እነ አቶ ሳሙኤል ካሮቱ ወይ ዱላው እንዲመዘዝ

የተቀመጡ የሚሏቸው) ነጥቦች ይዘት በዓላማው የተቀመጠውን «የሚጎለብት» ነገር ወይም ሂደት መኖር የሚያመለክትም ሆነ የሚቀበል አይደለም:: ለመጥቀስ ያህል ከተቀመጡት ሶስቱ የታሰሩ ሰዎችን (በዋናነት በፖለቲካ) አስመልክቶ ርእታዊ ዳኝነት፣ የመጎብኘት መብት እና መፈታት የሚጠይቅ ነው:: በማስከተልም የተዘረዘሩት «የፕሬስ ነፃነት፣ የምርጫ ቦርድ ነፃነት፣ የብሮድካስቲንግ ሚዲያ ፈቃድ መስጠት ወዘተ.» የሚሉ ናቸው:: እነዚህ ዝርዝሮች ያለ ግን በበቂ ደረጃ ያልተከናወነ ሂደትን አመልክተው ማጎልበትን በተከታይ ተግባርነት የሚያሳዩ አይደሉም:: ካለምንም ማሽሞንሞን ከተቀመጠ ታሳቢ አድርገው የተነሱት የሌሉ እና የሚፈጠሩ ናቸው የሚል የእውነታ ንባብ ነው:: በሌላ አባባል የብሮድካስት ሚዲያ ፈቃድ መስጠት የሚለው መስፈርት ወይም እርምጃ ታሳቢ ያደረገው እስከ አሁን አልተሰጠም ማለትን እንጂ የተሰጠው በቂ አይደለም ማለትን እንዳልሆነ ግልፅ ነው:: በተመሳሳይ የተጠቀሰው የፕሬስ፣ የዳኝነት፣ ... ነፃነትም ሆነ የእስረኞች መፈታት መነሻ ይኼው ነፃነት የለም፤ ያልተፈቱ እስረኞች አሉ የሚል የአርቃቂዎችን ቀድሞ የተያዘ ብይን ነው:: (ያልተፈቱት እስረኞች እንማን መሆናቸው ባይታወቅም እና ታስረው የነበሩ ተፈትተው አርቃቂዎቹን በማጀብ ላይ ቢገኙም):: ከዚህ አንፃር ሲታይ ረቂቁ ማጎልበት የሚለውን የዘነጋ ብቻ ሳይሆን ሊጎለብት የሚችል እና የተጀመረ የዴሞክራሲ፣ የመብት መከበር፣ የነፃ ዳኝነት ሂደት መኖሩን ሙሉ በሙሉ በመካድ የሚነሳ እና ግቡንም ከዜሮ መፍጠር ያደረገ ነው:: ፈጣሪዎቹ ደግሞ እነ እገሌ ባይባሉም የአሁኑ የኢትዮጵያ ስርዓትና መንግስት እንዳልሆነ ግልፅ ነው::

በሁለተኛ ደረጃ በዚህ ረገድ አስረጂ ሆኖ ሊጠቀስ የሚችል የረቂቅ ሰነዱ ይዘትም አለ:: ይኸውም ከአተገባበር በተያያዘ የሚያስቀምጣቸው ፅንሰ ኃሳቦች/ቁልፍ ቃላቶች የተገደበና ወጥነት ያለው የትርጉም ግልፅነት ችግር ያላቸው መሆኑ ነው:: የሚከተሉት በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላል:: ለምሳሌ፣ አቶ ዳግማዊ ተርጉመው እንዳስቀመጡት አርቃቂዎቹ ወደ ዱላው ለመሸጋገር መስፈርት ብለው ያስቀመጧቸውን አስራ አንድ ጉዳዮች አስመልክቶ ፈተናው የተሰጠው (እንዲወድቅ የሚፈለግ እና እንደሚወድቅም ታሳቢ የተደረገው) የኢትዮጵያ መንግስት «ተቀባይነት ያለው ጥረት» አድርጎ መሻሻሉን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት «አጥጋቢ ምስክርነት» መስጠት አለባቸው ይላል:: ጥያቄው አጥጋቢ ምንድነው? በማን መለኪያ? ምን? መቼና የት ተለክቶ ነው አጥጋቢ የሚባለው? «ተቀባይነት ያለው ጥረት» ማለት ምንድነው? በምንና በማን መስፈርትስ ሲሰፈር? (በኪሎ፣ በፓውንድ፣ በኩንታል፣ በተፈቀዱ ስብሰባዎች ብዛት፣ በሰልፎች...) ተፈታኙ የሚፈተነው አይኑን ታስሮ ብቻ ሳይሆን ለተፈተነው ፈተና ትክክለኛ የሚባል ወጥ መልስ በሌለበትና መኖር አለመኖሩንም በማያውቅበት ነው:: በመሆኑም እንደሚወድቅ ሳይታለም የተፈታ ይሆናል:: ይህ እንዳይሆን እንኳን በፈታኞቹም ረገድ ወጥና የተገደበ ማጣቀሻ አልተቀመጠም:: ከዚህ አኳያ የፕሬዚዳንቱ አጥጋቢ የሚሆነው ለማን ነው? ለፕሬዚዳንቱ? ሰነዱን ላረቀቁት የተለያየ ፍላጎት ያላቸው የአሜሪካ ፓርላማ ሶስት...አምስት ወይም ስድስት እንደራሴዎች? የታወቀ ነገር የለም::

«ለዴሞክራሲ ሂደት ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ብዙ ድርጅቶች ... የፋይናንስ፣ የስልጠና፣ ወዘተ. ድጋፍ መስጠት» አንደኛው በማስፈፀሚያ ፕሮግራምነት የተጠቀሰ ነው:: እዚህ ጋር ቁልፉ ጉዳይ ሆን ተብሎ  ፍሪ ሳይዝ (አሜሪካኖቹ እንደሚሉት) የሆነ ልክ እንዲኖራቸው ተደርገው የተቀመጡት ቃላቶች ናቸው፤ «<u>ትልቅ ሚና</u> የሚጫወቱ፣ <u>ብዙ ድርጅቶች</u>» ወዘተ.:: እነዚህ «ብዙ ድርጅቶች» የተጫወቱት ሚና ምንነትና ዓይነት ብቻ ሳይሆን ትልቅ መሆኑ በምን እንደሚሰፈርና በማን አረጋጋጭነት እንደሚረጋገጥ በግልፅ አልተቀመጠም:: ይብሱንም ይህን መሰል ትልቅ ሚና የሚጫወቱት ደግሞ በደፈናው ድርጅቶች ናቸው፤ ያውም ብዙ:: ይህ ከምን እስከምን ያሉ ድርጅቶችን እንደሚጨምር በዘርፍ፣ በተግባር አይነት፣ በህጋዊ ማንነት፣ በስራ መጠን፣ ወዘተ. በግልፅ ተገድቦ በረቂቁ

አልተቀመጠም። ምናልባት ማንኛውንም ምግብ ቤት፣ የእህል መሸጫ፣ የውበት ሳሎን፣ ቡቲክ፣ ዩኤስኤይድ፣ ፒስ ኮር፣ የመምህራን ማህበር፣ አስር ቦታ ተከፍሎ የውክልና ሽሚያ ያለበት ፓርቲ፣ የሰፈር ዕድር ወዘተ. ወዘተ. ሊጨምር ይችላል። ላይጨምርም ይችላል። ይህን የሚያውቀውና የሚወስነው አርቃቂው አሜሪካዊ እንደራሴና ጥቂት ታማኞች (ምናልባት) ሲሆኑ፤ ይህ የሚመለከታቸው ደግሞ ያሉት ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ራፐብሊክ ሉዓላዊ ግዛቶች ስር በሆነው የደቡብ፣ የአማራ፣ የሶማሌ፣ የቤንሻንጉል፣ የአፋር፣ የጋምቤላ፣ የትግራይ፣ የኦሮሚያ፣ ወዘተ. ክልሎች በሚገኙ ከተሞች ነው። እንግዲህ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና የዳያስፖራ አቻዎቻቸው የሆኑት ምሁራን ወንድሞቻችን በመከራከሪያነት የሚያነሱት «የሉዓላዊነት ተለጣጭ ትርጓሜ» ይህ የማይመለከተው ከሆነ በማጣቀሻነት የሚያቀርቡልን የፖለቲካ ሳይንስ መድብልም በእርግጥ የምንጋራው አይደለም።

ከእነዚህ መሰረታዊ ነጥቦች በመነሳት ሲታይ በኤች አር 2003 ዙሪያ የተወሰኑ ወንድሞቻችን/እህቶቻችን ተደጋግሞ የሚቀርበው «ከቀና አጋርነት የመነጨና ባለቤትነትንም ሆነ ሉዓላዊነትን የማይነካ» የሚባልለት የረቂቁ ይዘት አርቃቂዎቹ በመንደርደሪያነት ብቻ ተጠቅመው የጣሉት ወይም በጠቀስነው የአፈፃፀም ምርጫቸው ያፈረሱት ከመሆን ውጪ መቆሚያ የለውም። ይኑረው ከተባለም የነበር ቅዱስነትን ሙጭጭ ብሎ ከመሟዘዝ የዋህነት ያለፈ መቆሚያ ሊሰጡት የማይቻል ቸርነትን የሚፈትን ተግባር ነው። በእርግጥ የግለሰቦች ስሜት፣ እምነትና ማንነት ለዚህ የዋህ ሙጭጭ ባይነትና ቸርነት ሲባል ሊገበር ይችል ይሆናል። የአንድ ሀገር ህዝብ ሉዓላዊ ህልውና ግን ሊገበር ቀርቶ ሊሞከርም አይችልም። በህዝብና በሀገር ደረጃ «የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም» የሚለው ብሂል ተመራጭነትም፣ ተገቢ መሰረትም የለውምና።

በመሆኑም ኤች አር 2003 በአጋርነት ይቅርና በሙሉ ገባሪ ተገዢነት ለመተግበር ቢሞከር እንኳን የማይተገበር ነው። ምክንያቱም ሰፋሪዎቹ፣ አስፈፃሚዎቹ፣ ማረጋገጫው ድርጊትና አረጋጋጭ ዳኞቹ፣ ሁሉም አንድ እና አንድ የሆኑበት የግል ድግስና ፈተና ነውና። ምናልባት ይህን በሙሉ ባርነት ተቀብሎ መተግበር ይቻል ይሆናል። (እሱም በቂ አይደለም ተብሎ ሌላ ጥያቄ ካልታከለበት)። ይህ ግን ኢትዮጵያዊነትን ከኖሩና ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ለመጠየቅ እጅግ ይከብዳል። እንደምንም (እንደ አንዳንድ ወንድሞቻችን) መጠየቁ ሊደፈር ከቻሉ እንኳን አዎንታዊ ምላሽ የሚገኝለት ስለመሆኑ እጅግ እጅግ ያጠራጥራል።

በቀጣዩ ክፍል ለምን ይህ ሆነ? ውጤቱስ ምን ይሆናል? የደጋፊ ተከራካሪዎች ዋነኛ ጭብጦችስ ምን ይመስላሉ? የሚለውን ለመቃኘት እንሞክራለን። እስከዚያው ቸር ይግጠመን።